# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

# ሁለተኛው ትውልድ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም

### የቲቢና ስጋደዌ መከላከልና ቁጥጥር ስራዎች ፓኬጅ

ሐምሌ 2007 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ማውጫ


ክፍል አንድ፡ የቲቢ መከላከልና ቁጥጥር መርሐግብር ...... iii
1. መግቢያ ...... 1
2.1. አጠቃላይ ዓላማ ...... 2
2.1.1. ዝርዝር ዓላማዎች ...... 2
3. በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራትና አተገባበር ...... 2
3.1. የቀበሌውን የቲቢ በሽታ መጠንና ስርጭት ያገናዘበ የመከላከል ስራን እንዲሁም የህሙማን እንክብካቤ ዕቅድ ማዘጋጀትና መፈፀም ...... 2
3.2. ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን ማከናወን ...... 3
3.3. የቲቢ በሽታ ምልክት ያለባቸው ሰዎችን በመለየት ምርመራ እንዲያገኙ ማድረግ፤ ...... 4
3.3.1. ከሕሙማን ጋር አብረው በመኖራቸው ምክንያት ለቲቢ በሽታ የተጋለጡ ሰዎችን የምርመራ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፡ ...... 4
3.3.2. ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ የሚገኝባቸው ሰዎች የቲቢ በሽታ ምርመራ እንዲያገኙ ማድረግ፤ ...... 5
3.3.3. በመኖሪያ አካባቢያቸው ምክንያት ተከታታይ የቲቢ ምርመራ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሠብ ክፍሎች ለይቶ የቲቢ ምርመራ እንዲያገኙ ማድረግ ...... 5
3.3.4. ለፀረ-ቲቢ መድኃኒቶች የተላመደ ቲቢ የተጋለጡ ሰዎችን በመለየት ተገቢውን ምርመራ እንዲያገኙ ማድረግ፤ ...... 5
3.4. የቲቢ ህክምና መስጠት ...... 6
3.4.1. የቲቢ ሕሙማን ተገቢውን ሕክምና በአቅራቢያቸው እንዲያገኙ ማድረግና መከታተል (Community DOT)፣ ...... 6
3.4.2. የፀረ-ቲቢ መድኃኒቶችን የተላመደ ቲቢ ሕሙማን መድኃኒታቸውን በአግባቡ እንዲወስዱ ማድረግና ሁሉን አቀፍ የሆነ ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ ...... 7
3.4.3. ለቲቢ ሕሙማን በሕክምና ወቅት የሚደግፏቸውን ሰዎች ማዘጋጀትና በክትትል ሥራ ላይ ማሳተፍ፣ ...... 7
3.5. የቲቢ መከላከል፤ ቁጥጥርና ክብካቤ ሥራን መመዝገብ፤ መረጃውን በማደራጀት ሪፖርት ማጠናቀርና መላክ፤ በግብአትነት ጥቅም ላይ ማዋል ...... 8
3.6. አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ...... 8
የህክምና ግብዓቶችና ሌሎች ቁሣቁሶች ...... 8
3.7. የጤና ጣቢያ ጤና ኬላ ትስስር ...... 9
3.8. የሚጠበቅ ውጤት ...... 9
3.8.1. የክትትል፤ግምገማ ና ዋና ዋና መለኪያዎች ...... 10
3.8.2. ክትትልና ግምገማ ...... 10
3.8.3. ዋና ዋና አመላካቾች ...... 11
ቁልፍ መልዕክቶች ...... 12
ክፍል ሁለት፡ የስጋደዌ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር መርሐ ግብር ...... 15
1. መግቢያ ...... 16
2. ዓላማ ...... 17
2.1. አጠቃላይ ዓላማ ...... 17
2.1.1. ዝርዝር ዓላማዎች ...... 17
3. ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራትና አተገባበር ...... 17

3.1. የሥጋ ደዌ በሽታ መጠንና ስርጭት ያገናዘበ የመከላከል፣ቁጥጥር፣ ሕክምና የህሙማን ክብካቤ ዕቅድ ማዘጋጀትና መፈፀም ........ 17
3.2. ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን ማከናወን ........ 18
3.3. የሥጋደዌ በሽታ ምልክቶች ያለባቸው ሰዎችን በመለየት ምርመራ እንዲያገኙ ማድረግ፤ ........ 19
3.3.1. ከሕሙማን ጋር አብረው በመኖራቸው ምክንያት ለሥጋ ደዌ በሽታ የተጋለጡ ሰዎችን የምርመራ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፡ ........ 19
3.3.2. የሥጋ ደዌ ሕሙማን ተገቢውን ሕክምና በአቅራቢያቸው እንዲያገኙ ማድረግና መከታተል፣ ........ 19
4. አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ........ 20
4.1. የህክምና ግብዓቶችና ሌሎች ቁሣቁሶች ........ 20
4.2. የጤና ጣቢያ ጤና ኬላ ትስስር ........ 20
4.3. የሚጠበቅ ውጤት ........ 21
4.4. የክትትልና ግምገማ፤ የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ዋና ዋና አመላካቾች ........ 22
4.4.1. ክትትልና ግምገማ ........ 22
4.4.2. የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ዋና ዋና አመላካቾች ........ 22

# ክፍል አንድ፡ የቲቢ መከላከልና ቁጥጥር መርሐግብር

# 1. መግቢያ

ቲቢ በዋነኛነት ማይኮባክቴሪየም ቲዩበርክሎሲስ ተብሎ በሚጠራ የባክቴሪያ ዝርያ አማካኝነት የሚከሰት በሽታ ነው፡፡ በሽታው ማንኛውንም የሰውነት ክፍል ያጠቃል፤ ሆኖም በቲቢ ከሚጠቁት የሰውነት ክፍሎች ሰማኒያ ከመቶው የሚሆነው ሳንባ ሲሆን ቀሪው ሃያ ከመቶ ከሳንባ ውጪ የሆኑ የአካል ክፍሎች ናቸው፡፡ በሽታው ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍሎች ያጠቃል፤ ይሁን እንጂ በቲቢ በበለጠ የሚጠቁት ዕድሜያቸው ከ15-50 ዓመት የሆኑት አምራችና የቤተሰብ ኃላፊነት ያላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ በሽታው በአንድ አገር ላይ የሚያደርሰው ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡

የቲቢ በሽታ በየትኛውም የዓለም ክፍል ተሠራጭቶ የሚገኝ ስሆን አገራችን ኢትዮጵያ በቲቢ በሽታ በከፍተኛ ደረጃ ከተጠቁት አገሮች ዝርዝር ዉስጥ ትገኛለች፡፡ እንዲህ ዓይነት ልዩ ትኩረት የሚሹ የጤና ችግሮችን ለመቅረፍ ዋነኛው መሣሪያ በአሁኑ ጊዜ ውጤታማ እየሆነ ያለውን የጤና ኤክስቴንሽንና የልማት ሠራዊት ሥልትን መጠቀም ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ዙሪያ ፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት ይህንን የተፈጠረውን አመቺ ሁኔታ የቲቢ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዎችን ለማሳካት በበቂ መጠን ተጠቅመውበታል ለማለት አያስደፍርም፡፡ አመርቂ ውጤት ያስመዘገቡ ሌሎች የጤና ፕሮግራሞች ተሞክሮ እንደሚያሳየን እነዚህን ሥልቶች በአግባቡ በመጠቀም የቲቢ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር አገልግሎትን በቀላሉ ወደ ሕብረተሰቡ ብሎም ወደ ቤተሰብ ደረጃ በማውረድ እንዲሁም የአገልግሎት ዓይነቱንና ጥራቱን በመጨመር የታቀዱትን ግቦች ማሣካት ይቻላል፡፡

በዚህም መሠረት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን በማሰልጠንና በመመደብ፤ በማህበረሠብ ደረጃ መከናወን ያለባቸውን የቲቢ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራትን በመፈፀም እንዲሁም የህክምናና እንክብካቤ አገልግሎት ለህብረተሠቡ ቅርብ በሆኑ ጤና ኬላዎች በመስጠት የህብረተሠቡን ተሣታፊነትና የአገልግሎቶቹ ተጠቃሚነትን መጨመር ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የህክምናና እንክብካቤ አገልግሎቶች በቅርበት እንዲሠጡ በመደረጉ የጤና አገልግሎትን ለማግኘት በሚደረግ ጉዞ ምክንያት የሚጠፋውን ጊዜ፤ ጉልበትና የገንዘብ ወጪ ስለሚያስቀር የህብረተሠቡን ከጤና አገልግሎት ጋር የተያያዘ ወጪን ይቀንሣል፤ በጤና ጣቢያና ሆስፒታል ላይ የሚደርሠውንም የስራ ጫና ይቀንሣል፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የማህበረሠብ አቀፍ የቲቢ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር ስራውን የመምራት፤ የማስተባበርና የመፈፀም ኃላፊነት መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ስለዚህ የቲቢ በሽታ ስርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር፣ አገልግሎቱን የበለጠ ለማጠናከርና ከዚህ በፊት ከነበረው ማህበረሰብ አቀፍ የቲቢ መከላከልና መቆጣጠር በተጨማሪ መድኃኒት የተላመደ ቲቢ መከላከልና መቆጣጠር በሁሉም አካባቢዎች በስፋት ለማዳረስ እንዲቻል ይህ የሁለተኛ ትውልድ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የቲቢ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር ፓኬጅ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

## 2. ዓላማ

### 2.1. አጠቃላይ ዓላማ

ህብረተሠቡን በማሣተፍ የቲቢ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራትን በማከናወንና ለቲቢ ህሙማን እንክብካቤ በማድረግ የበሽታውን ሥርጭት መግታት፣ በሽታው የሚያደርሰውንም ሕመም፣ ሞትና የአካል ጉዳት መቀነስ፤ መቆጣጠር ብሎም በቀጣይ የሕብረተሰቡ ችግር ከማይሆንበት ደረጃ ላይ ማድረስ ነው።

#### 2.1.1. ዝርዝር ዓላማዎች

- ህብረተሰቡ በቲቢ በሽታ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግና በመከላከልና ቁጥጥር ሥራው ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆን ማስቻል፤
- የቲቢ በሽታ ምልክት የታየባቸው ሰዎችን በቶሎ በመለየትና አገልግሎቱ ወደ ሚገኝበት ጤና ተቋም በመላክ ተገቢውን ምርመራ እንዲያደርጉ ማስቻል፣
- የቲቢ ሕሙማን ቤተሰቦችንና በተለየ ሁኔታ ለቲቢ በሽታ የተጋለጡ የህብረተሠብ ክፍሎች ተገቢውን ምርመራ ህክምናና ክትትል እንዲያገኙ ማስቻል፤
- የቲቢ እለታዊ የመድኃኒት ሕክምናና ክትትል አገልግሎትን በሁሉም ጤና ኬላዎች እንዲሰጥ በማድረግ አገልግሎቱን የበለጠ ተደራሽና ስኬታማ ማድረግ፣
- ህብረተሠቡንና የቲቢ ሕሙማን ደጋፊዎችን ዝግጁ አድርጎ በሕክምና ክትትሉ ላይ በማሳተፍ፣እንዲሁም የክትትል አገልግሎቱን ጠንካራ በማድረግ የፀረ-ቲቢ መድኃኒቶችን የተላመደ ቲቢ ሥርጭትን መግታት፣
- በማህበረሰብ ደረጃ የሚከናወኑትን የቲቢ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራትን እንዲሁም የሚሠጡትን የቲቢ ምርመራ፤ ህክምናና ክትትል አገልግሎቶችን በመመዝገብ፤ መረጃዎችን በመተንተንና ሪፖርቶችን በማጠናቀር ለውሣኔ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፤

## 3. በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራትና አተገባበር

### 3.1. የቀበሌውን የቲቢ በሽታ መጠንና ስርጭት ያገናዘበ የመከላከል ስራን እንዲሁም የህሙማን እንክብካቤ ዕቅድ ማዘጋጀትና መፈፀም

- በማህበረሠብ ደረጃ የሚገኙ የቲቢ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር መርሃ ግብርን ለማቀድና አፈፃፀሙን ለመከታተል የሚረዱ የጤናና የሥነ ሕዝብ መረጃዎችን ማሰባሰብ፤ ማደራጀትና መተንተን፤
- ቀደም ባሉ ጊዜያት በአካባቢው የተለዩ የቲቢ ህሙማንን ዝርዝር መረጃ መሠብሠብ፤ ማደራጀትና መተንተን፤ ውጤቱንም ለዕቅድ ዝግጅት በግብዓትነት መጠቀም፤

- ❖ ከጤናው ዘርፍና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ሊቀርቡ የሚችሉ ግብአቶችን መረጃ ማሠባሠብና መተንተን፤ ውጤቱንም ለዕቅድ ዝግጅት በግብዓትነት መጠቀም፤
- ❖ የመረጃ ትንተና ውጤትን መሠረት በማድረግ የቲቢ መከላከልና መቆጣጠር ስራዎችን እንዲሁም የቲቢ ህሙማን እንክብካቤ ዕቅድ ማዘጋጀት፤
- ❖ በዕቅድ ዝግጅት ወቅት በቀበሌው ዉስጥ ያሉ ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ፤ በዕቅድ ዝግጅትና አተገባበር ላይ ሙያዊ ድጋፍ መስጠትና ክትትል ማድረግ፤
- ❖ ከህብረተሠቡና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ዕቅዱን መፈፀም፤ አፈፃፀሙን መከታተልና መገምገም፤

## 3.2. ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን ማከናወን

- ❖ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ለቲቢ ሕሙማን፣ ለቤተሰቦቻቸውና ለሕብረተሰቡ በቲቢ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር ተግባራት ላይ ተከታታይነት ያለው ትምህርት መስጠት፣
- ❖ በቲቢ መድኃኒት አወሳሰድና በበሽታው ቁጥጥር ዙሪያ ለሕሙማን ቤተሰብ አባላት፣ ለሕሙማን ደጋፊዎች፣ ለልማት ሰራዊት  አባላት ሥልጠና መስጠትና አፈጻጸሙን መከታተል፤
- ❖ በትምህርት ቤቶች፤ በልማት ተቋማት፤ በማረሚያ ቤቶች በመገኘት ለተቋሙ ህብረተሠብ በቲቢ በሽታ መተላለፊያ መንገዶች፤ የበሽታው ምልክቶች፤ ህክምናውና መከላከያ መንገዶቹ ላይ ያተኮረ የጤና ትምህርት መስጠት፤
- ❖ በትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ጋር በመተባበር ተማሪዎች ለቤተሠባቸውና በዙሪያቸው ለሚገኙ ማህበረሠብ ስለ ቲቢ በሽታ መተላለፊያ መንገዶች፤ መከላከያና ቁጥጥር ዘዴዎች አውቀው እንዲያስተምሩ ማስቻል፤
- ❖ መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት አባላትና ሠራተኞች በቲቢ መከላከልና ቁጥጥር ላይ ያተኮረ የጤና ትምህርት መስጠት፤
- ❖ ከቀበሌ አመራርና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የቲቢ ቀን በቀበሌ ደረጃ እንዲከበር ማስተባበርና መምራት፤ በዝግጅቱም ላይ ቲቢ ላይ ያተኮሩ መልዕክቶች እንዲተላለፉ ማድረግ፤
- ❖ የቲቢ ህሙማን በተቻለ መጠን የተመጣጠነ ምግብ እንዲመገቡ፤ የህሙማን ቤተሠቦችም ለዚሁ እንዲተባበሩ የጤና ትምህርት ማስተላለፍ፤
- ❖ ቤተሠቦች በተለይም እናቶች አዲስ የሚወለዱ ህፃናት የቢሲጂ ክትባት በወቅቱ እንዲያገኙ ስለክትባቱ ጥቅም በቂ መረጃ መስጠት፤

**የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይቶች የሚከናወኑባቸው ቦታዎችና ሁኔታዎች:**

- ❖ በቤት ለቤት ጉብኝት ወቅት
- ❖ ህብረተሠቡ የጤና አገልግሎት ለማግኘት ወደ ጤና ኬላ በሚመጣበት ወቅት

- ከቲቢ በሽታ ጋር ተዛምዶ ያላቸው በሽታዎች ላይ የጤና ትምህርት በሚሠጥበት ወቅት ለምሣሌ፡ ኤች.አይ.ቪ፤ የመተንፈሻ አካላት በሽታዎች፤ የአካባቢ ንፅህና፤ ክትባት

- በተለያዩ ስብሠባዎች ላይ

- በገበያ ቦታዎች ላይ

- በአንድ ለአምስትና የልማት ቡድን ስብሠባዎች ላይ

- በትምህርት ቤቶች፤ ማረሚያ ቤቶች

## 3.3. የቲቢ በሽታ ምልክት ያለባቸው ሰዎችን በመለየት ምርመራ እንዲያገኙ ማድረግ፤

- የልማት ቡድኖች፤ የ1ለ5 ትስስር አባላት በአጠቃላይ ማህበረሠቡ የለዩአቸውን የቲቢ በሽታ ምልክት ያለባቸውን ሠዎች በጤና ኬላ ተቀብሎ ለቲቢ በሽታ ምርመራ ማድረግና ተጨማሪ ምርመራ የሚያስፈልጋቸውን በመለየት ወደ ጤና ጣቢያ መላክ፤

- በቤት ለቤት ጉብኝት፤ በገበያ ቦታዎች፤ በትምህርት ቤቶች፤ በእምነት ተቋማት፤ በማረሚያ ቤቶች፤ በልማት ተቋማት ወዘተ… በሚሄዱበት ወቅት የለዩዋቸውን የቲቢ ምልክት ያለባቸውን ሰዎች ለምርመራ ወደ ጤና ጣቢያመላክ፤

### 3.3.1. ከሕሙማን ጋር አብረው በመኖራቸው ምክንያት ለቲቢ በሽታ የተጋለጡ ሰዎችን የምርመራ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፡

- ከቲቢ ሕሙማን ጋር የሚኖሩ የቤተሰብ አባላትን መጎብኘትና የበሽታው ምልክት ያለባቸውን ሠዎች በመለየት መመርመር፤

- የቲቢ በሽታ ምልክት ለሚያሳዩና ተጨማሪ ምርመራ የሚያስፈልጋቸውን የቲቢ ታማሚ ቤተሰብ አባላት በመለየት ወደ ጤና ጣቢያ መላክ፣

- ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናትና አረጋውያን የቲቢ ሕመምተኛ ቤተሰብ አባላት የበሽታውን ምልክት ባያሳዩም ለቲቢ ምርመራ ወደ ጤና ጣቢያ መላክ፣

- ከቲቢ ሕመምተኛ ቤተሰብ አባላት ውስጥ በሌሎች የሰውነት በሽታ መከላከል አቅምን በማዳከም ለቲቢ በሽታ ሊያጋልጡ የሚችሉ ተጓዳኝ የጤና ችግሮች ለምሳሌ የስኳር በሽታ ያለባቸውን ሰዎች ለምርመራ ወደ ጤና ጣቢያ መላክ፣

- በደማቸው ውስጥ ኤች. አይ. ቪ. ያለባቸው የቲቢ ሕመምተኛ ቤተሰብ አባላት የቲቢ በሽታ ምልክት ባያሳዩም ለቲቢ ምርመራ ወደ ጤና ጣቢያ መላክ፣

### 3.3.2. ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ የሚገኝባቸው ሰዎች የቲቢ በሽታ ምርመራ እንዲያገኙ ማድረግ፤

- ❖ ኤች. አይ. ቪ. በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሰዎችን በመለየት በተገቢው መንገድ ለቲቢ ምርመራ ማድረግ፤ የቲቢ በሽታ ምልክት የሚያሣዩትን በመለየት ለተጨማሪ ምርመራ ወደ ጤና ጣቢያ መላክ፤
- ❖ የምርመራው ውጤቱን መከታተል፤ በውጤቱም መሠረት ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ፤ ህክምናቸውንም በአግባቡ መውሠዳቸውን መከታተል፤

### 3.3.3. በመኖሪያ አካባቢያቸው ምክንያት ተከታታይ የቲቢ ምርመራ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሠብ ክፍሎች ለይቶ የቲቢ ምርመራ እንዲያገኙ ማድረግ

- ❖ በጤና ተቋም የቲቢ በሽታ እንዳለበት ከተረጋገጠለት ተማሪ ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ለነበሩ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤቱ በመሄድ ለቲቢ ምርመራ ማድረግ፤ ተጨማሪ ምርመራ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች በመለየት ወደ ጤና ጣቢያ መላክ፤
- ❖ ከቲቢ ህመምተኛ ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ሲማሩ ለነበሩ ተማሪዎች ተገቢውን ክትትል ማድረግ፤
- ❖ በአካባቢው በሚገኙ ማረሚያ ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ ታራሚዎችና ሠራተኞች ተከታታይ የሆነ የቲቢ ምርመራ ማድረግ፤ ተጨማሪ ምርመራ የሚያስፈልጋቸውን በመለየት ወደ ጤና ጣቢያ መላክ፤

### 3.3.4. ለፀረ-ቲቢ መድኃኒቶች የተላመደ ቲቢ የተጋለጡ ሰዎችን በመለየት ተገቢውን ምርመራ እንዲያገኙ ማድረግ፤

- ❖ የቲቢ በሽታ ህክምናን እየወሠዱ የመሻል ስሜት የማይሠማቸው ወይም በጎ ለውጥ ያላሣዩ ታካሚዎችን በመለየት ክትትል ማድረግ፤ ተጨማሪ ምርመራ የሚያስፈልጋቸውን ወደ ጤና ጣቢያ መላክ፤
- ❖ የፀረ-ቲቢ መድኃኒቶችን የተላመደ ቲቢ እንዳለባቸው በጤና ተቋም ተረጋግጦ መድኃኒት እየወሠዱ የሚገኙ ታካሚዎች ቤተሠቦችን በሙሉ ለምርመራ ወደ ጤና ጣቢያ መላክ፤
- ❖ በስራ ወይም በሌሎች ሁኔታዎች ከፀረ ቲቢ መድኃኒቶችን የተላመደ ቲቢ ህመምተኛ ጋር ለረጂም ጊዜ ቆይታ ያደረጉ ሠዎችን ለይቶ ለምርመራ ወደ ጤና ጣቢያ መላክ፤

## 3.4. የቲቢ ህክምና መስጠት

### 3.4.1. የቲቢ ሕሙማን ተገቢውን ሕክምና በአቅራቢያቸው እንዲያገኙ ማድረግና መከታተል (Community DOT)፣

- የቲቢ በሽታ እንዳለባቸው ለተረጋገጠላቸው ታካሚዎች ሁሉ ሕክምናቸውን እስኪጨርሱ ድረስ ሊያገኙ የሚገባቸውን የመድኃኒት ዓይነትና መጠን ምርመራቸውን ካደረጉበት ጤና ጣቢያ በመረከብ የህክምና አገልግሎቱን በጤና ኬላ እንዲቀጥሉ ማድረግ፤
- ሕክምናቸውን በጤና ኬላ ለሚከታተሉ የቲቢ ሕሙማን በስማቸው የመጣላቸውን መድኃኒት በታዘዘው መጠንና ጊዜ መሠረት መስጠትና መውሠዳቸውን ማረጋገጥ፤
- ሕክምና ላይ ያሉ የቲቢ ሕሙማንን ወደ መኖሪያ ቤታቸው በመሄድ የጤንነታቸውን ሁኔታ መከታተል እንዲሁም ለሚታይባቸዉ የጤና ችግር ዕርዳታ እንዲደረግላቸው ወደ ጤና ጣቢያ በመላክ ግብረ መልስ መቀበል፤
- የታዘዘላችዉን የቲቢ መድኃኒት በደጋፊዎች ክትትል ለሚወስዱ የቲቢ ሕሙማን ከደጋፊዎቻቸው ጋር በመገናኘት መድኃኒታቸውን በየዕለቱ በአግባቡ መውሰዳቸውን ማረጋገጥ፤
- በህሙማን ደጋፊ ክትትል የቲቢ ህክምና የሚወስዱ የቲቢ ታካሚዎች መድኃኒቶቻቸውን እስኪጨርሱ ድረስ ለደጋፊዎቻቸው የቅርብ ክትትልና ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፤
- የቲቢ ታካሚዎች ከሚወስዱት መድኃኒት ጋር በተያያዘ ቀላል ወይም ከባድ የሆነ የመድኃኒት የጎንዮሽ ችግር መከሰት አለመከሰታቸውን መከታተል፤ ከተከሰቱ በመመሪያው መሠረት መወሰድ የሚገባውን እርምጃ መውሰድ፣
- የቲቢ ሕክምናቸውን በግል ጤና ተቋማት መከታተል ለሚፈልጉ ወይም መከታተል ለጀመሩ የቲቢ በሽታ ህሙማን የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍና ክትትል እንዲያገኙ ማድረግ፤
- በቲቢ ሕክምና ሥርዓት መሠረት መድኃኒቶቻቸውን እየወሰዱ ለድጋሚ የአክታ ምርምራ ቀጠሮ የተሰጣቸውን በሙሉ ወደ ጤና ጣቢያ መላክ ወይንም እንደ አስፈላጊነቱ ከጤና ጣቢያው የላቦራቶሪ ቴክኒሽያን በፕሮግራም መጥቶ ናሙና ሰብስቦ የሚሄድበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- በሕክምና ላይ የሚገኙ የቲቢ ሕመምተኞች በሙሉ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፤
- ታካሚዎች የአድራሻ ለውጥ የሚያደርጉ ከሆነ በሚሄዱበት ቦታም ሲደርሱ ሕክምናቸዉን ሳያቋርጡ መቀጠል እንዲችሉ መሸኛ እንዲዘጋጅላቸው ሕክምናቸውን ወደ ጀመሩበትና ክትትል ወደሚያደርጉበት ጤና ጣቢያ መልሶ መላክ፤

- ሕክምና የጀመሩ የቲቢ ሕሙማን ሕክምናቸውን ቢያቋርጡ ወደ መኖሪያ ቤታቸው በመሄድና በመወያየት ሕክምናቸውን እንዲቀጥሉና እንዲያጠናቅቁ ድጋፍ ማድረግ፤
- አዲስ የሚወለዱ ህፃናት የቢሲጂ ክትባት መውሠዳቸውን ማረጋገጥ ያልወሠዱትን ለይቶ ክትባቱን መስጠት፤
- በጤና ተቋም በቲቢ በሽታ አለመታመማቸው ተረጋግጦ የቲቢ በሽታ መከላከያ የታዘዘላቸው ሠዎች መድኃኒቱን በየዕለቱ መውሠዳቸውን መከታተልና እንዲወስዱ መደገፍ፤

### 3.4.2. የፀረ-ቲቢ መድኃኒቶችን የተላመደ ቲቢ ሕሙማን መድኃኒታቸውን በአግባቡ እንዲወስዱ ማድረግና ሁሉን አቀፍ የሆነ ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

- የፀረ-ቲቢ መድኃኒቶችን የተላመደ ቲቢ ሕሙማን መድኃኒታቸውን በየዕለቱ መውሰዳቸውን ማረጋገጥ፤ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉን አቀፍ ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸትና ድጋፉን እያገኙ መሆኑን መከታተል፤
- ሕክምና ላይ ያሉ የፀረ-ቲቢ መድኃኒቶችን የተላመደ ቲቢ ሕሙማን በየቀጠሮ ቀናቸው ወደ ሕክምና ጣቢያቸው በመሄድ ምርመራና የሕክምና ክትትል ማድረጋቸውን ማረጋገጥ፤
- የፀረ-ቲቢ መድኃኒቶችን የተላመደና ኤች.አይ.ቪ መድኃኒቶችን በመውሠዳቸው ጋር በተያያዘ ቀላል ወይም ከባድ የሆነ የመድኃኒት የጎንዮሽ ችግር መከሰት አለመከሰታቸውን መከታተል፤ ከተከሰቱ በመመሪያው መሠረት መወሰድ የሚገባውን እርምጃ መውሰድ፣
- በቲቢ ሕክምና ሥርዓት መሠረት መድኃኒቶቻቸውን እየወሰዱ ያሉ የፀረ-ቲቢ መድኃኒቶችን የተላመደ ቲቢ ሕሙማን ለክትትል የአክታ ምርምራ በቀጠሮ ጊዜያቸው ህክምናቸውን ወደሚያደርጉበት ጤና ተቋም መላክ፤
- ኤች. አይ. ቪ. በደማቸው ውስጥ የሚገኝባቸው የፀረ-ቲቢ መድኃኒቶችን የተላመደ ቲቢ ሕሙማን የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድኃኒት ሕክምና እንዲያገኙ ማድረግ፤
- ኤች. አይ. ቪ. በደማቸው ውስጥ ያለባቸው የፀረ-ቲቢ መድኃኒቶችን የተላመደ ቲቢ ሕሙማን የፀረ-ኤች. አይ. ቪ. መድኃኒት እየወሰዱ መሆናቸውን ተከታትሎ ማረጋገጥ፤

### 3.4.3. ለቲቢ ሕሙማን በሕክምና ወቅት የሚደግፏቸውን ሰዎች ማዘጋጀትና በክትትል ሥራ ላይ ማሳተፍ፣

- ስለ ደጋፊዎች ጠቀሜታ ህብረተሰቡን በተለይም ደግሞ የቲቢ ሕመምተኛና ቤተሰቦቹን ማሳወቅ፤
- የቲቢ ሕሙማን ደጋፊዎች ማሟላት ስላለባቸው መመዘኛዎች ከቲቢ ህሙማን ጋር በዝርዝር መወያየትና መስማማት፣

- ለቲቢ ሕሙማን ደጋፊነት የተመረጡትን ሰዎች ስለሚጠበቅባቸው ኃላፊነትና ስለ ቲቢ እና የፀረ-ቲቢ መድኃኒቶችን የተላመደ ቲቢ ሕክምና በቂ መረጃ እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- የተመረጡትን ደጋፊዎች በህሙማኑ ድጋፍ ሥራ ላይ ማሳተፍና አፈጻጸሙን መከታተል፡፡

## 3.5. የቲቢ መከላከል፤ ቁጥጥርና ክብካቤ ሥራን መመዝገብ፤ መረጃውን በማደራጀት ሪፖርት ማጠናቀርና መላክ፤ በግብአትነት ጥቅም ላይ ማዋል

- የተሰጡ የቲቢ ምርመራና እንክብካቤ አገልግሎቶችን፣ ያገልግሎቱ ተጠቃሚዎችን ዝርዝር መረጃ እንዲሁም የተከናወኑ የመከላከል እና ቁጥጥር ተግባራትን በተሟላ ሁኔታ መመዝገብ፣
- የተሠበሠበውን መረጃ በየወቅቱ ማደራጀትና መተንተን፤ የተገኘውን የመረጃ ትንተና ውጤት ለስራ አፈፃፀም ግምገማና ለዕቅድ ዝግጅት/ክለሣ በግብአትነት መጠቀም፤
- የተደራጀውን መረጃ መሠረት በማድረግ በየወቅቱ ሪፖርት ማጠናቀርና ለሚመለከታቸው አካላት ማስተላለፍ፤
- የተሠበሠቡና የተደራጁ መረጃዎችንና ሪፖርቶችን በአግባቡና በጥንቃቄ መያዝና መጠቀም፣

## 3.6. አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

### የህክምና ግብዓቶችና ሌሎች ቁሣቁሶች

በጤና ኬላ ደረጃ የሚከናወኑ የቲቢ መከላከልና ቁጥጥር ስራዎችና የሚሠጡት አገልግሎቶችን በተቀላጠፈና ጥራቱን በጠበቀ መንገድ ለማከናወን የሚደግፉ ሠነዶች፡

- የማዳመጫ መሣሪያ (Stethoscope)
- የደም ግፊት መለኪያ መሣሪያ
- የሠውነት ሙቀት መለኪያ
- የክብደት መለኪያ ሚዛን
- የ4 መድኃኒቶች ውህድ = ሪፋምፒሲን+አይ.ኤን.ኤች+ፓራዚንአማይድ+ ኢታንቡቶል ……….(RHZE)
- የ3 መድኃኒቶች ውህድ = ፋምፒሲን+አይ.ኤን.ኤች+ፓራዚንአማይድ .........(RHZ)
- የ2 መድኃኒቶች ውህድ =ሪፋምፒሲን+አይ.ኤን.ኤች .................................. (RH)
- የ2 መድኃኒቶች ውህድ = ኢታንቡቶል+አይ.ኤን.ኤች ................................ (EH)

በተናጠል መልክ በአገራችን እየተጠቀምንባቸው ያሉ መድኃኒቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ኢታንቡቶል (E)
- አይ. ኤን. ኤች (አይሶኒያዛይድ) (H) እና
- እስትሬፕቶማይሲን (S) ናቸው፡፡
- ለቲቢ በሽታ የምርመራ አገልግሎት የሚውሉ መዛግብት፣ ካርዶችን፣ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጾች፣ለምርመራ ወደ ሌላ ጤና ተቋም መላኪያ ቅፅ
- የማህበረሠብ አቀፍ ቲቢና ስጋደዌ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር አተገባበር መመሪያ፣
- ለልማት ሠራዊት አባላት፤ ለቲቢ ህሙማን፣ ለቤተሠቦቻቸውና ለትምህርት ቤቶች የተዘጋጀ አጭር መፅሐፍና በራሪ ፅሁፍ፣
- ለአዋቂዎችና ለህጻናት በውህድ መልክ የተዘጋጁ የቲቢ መድኃኒቶች ዓይነትና መጠን የምገልፅ ሠንጠረዥ፣
- የፀረ-ቲቢ መድኃኒቶች የሚያስከትሉት የጎንዮሽ ጠንቆች እና መወሰድ የሚገባው እርምጃ ለመግለፅ የተዘጋጀ ሠንጠረዥ፣
- በቲቢ ላይ መልዕክት ለማስተላለፍ የተዘጋጀ ፖስተር፣

## 3.7. የጤና ጣቢያ ጤና ኬላ ትስስር

በጤና ኬላ ደረጃ የማይሠጡ የአክታና ሌሎች ናሙናዎች ምርመራ እንዲሁም ሌሎች ተጨማሪ ምርመራዎች የሚያስፈልጓቸውን ህሙማን ጤና ኬላውን ወደሚደግፈው ጤና ጣቢያ እንዲሄዱ ይደረጋል፡፡ የተፈለገው የምርመራ አገልግሎት ለህሙማኑ መሠጠቱን ክትትል ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በምርመራው ውጤት መሠረት የህክምናና ክትትል አገልግሎት ህሙማኑ እንዲያገኙ የጤና ኬላውና ጤና ጣቢያው በቅንጅት ይሠራሉ፡፡ ጤና ጣቢያዎች በትስስሩ ለሚደግፏቸው ጤና ኬላዎች ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት የሚመደቡ ባለሙያዎችም በጤና ኬላ ደረጃ የሚሠጡ የቲቢ ምርመራ፤ ህክምናና ክትትል አገልግሎቶች ጥራታቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

ጤና ጣቢያዎች በጤና ኬላ ደረጃ ህክምናቸውን ለሚከታተሉ ህሙማን የሚሆኑ የቲቢ መከላከያና ህክምና መድኃኒቶችን በአቅራቢያቸው ለሚገኝ ጤና ኬላ እንዲደርስ ያደርጋሉ፤ በተለያዩ ምክንያቶች በትርፍነት የሚቀሩ የቲቢ መድኃኒቶችን ይረከባሉ፡፡ የቲቢ መከላከልና መቆጣጠር ተግባራትን አስመልክቶ በጤና ኬላ የተከናወኑ ስራዎችን ሪፖርት በየወቅቱ ተረክበው ይተነትናሉ፤ ከሚደግፏቸው ጤና ኬላዎች ጋር በመሆን አፈፃፀሙን ይገመግማሉ፤ ለአፈፃፀሙ መሻሻል የሚረዱ የእርምት ተግባራትን ይጠቁማሉ፤ መተግበራቸውንም ይከታተላሉ፡፡

## 3.8. የሚጠበቅ ውጤት

በጤና ኬላ ደረጃ የሚያስፈልጉ የሠው ኃይልና ሌሎች ግብዓቶች እንዲሟሉ በማድረግ እንዲሁም ተገቢውን ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት ጤና ኬላው የሚከተሉትን ውጤቶች እንዲያሣካ ይጠበቃል፡-

- ❖ ህብረተሠቡ የቲቢ በሽታ ስርጭትን ለመግታት የመከላከያ ዘዴዎችን ይተገብራል
- ❖ ጤና ኬላና ጤና ጣቢያ በመሄድ የቲቢ ምርመራና ህክምና አገልግሎት የሚያገኙ ሠዎች ቁጥር ይጨምራል
- ❖ የቲቢ ህሙማን ቤተሠቦች በሙሉ ለቲቢ በሽታ ምርመራ አገልግሎት ያገኛሉ
- ❖ ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ያለባቸው ሠዎች በሙሉ በየወቅቱ የቲቢ ምርመራ አገልግሎትና አስፈላጊውን ህክምና ያገኛሉ
- ❖ እድሜአቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ የቲቢ ህመምተኛ ቤተሠቦች የቲቢ ምርመራ አገልግሎትና የመከላከያ ህክምና ያገኛሉ
- ❖ ለቲቢ በሽታ በተለየ ሁኔታ የተጋለጡ ሠዎች የቲቢ ምርመራና ህክምና ያገኛሉ
- ❖ የቲቢና መድኃኒት የተላመደ ቲቢ ህክምና የጀመሩ ህሙማን በሙሉ ህክምናቸውን በተሣካ ሁኔታ ያጠናቅቃሉ

በአጠቃላይ የቲቢ በሽታ ስርጭትን በመከላከል ህሙማንን በወቅቱ በመለየት፤ በመመርመርና በማከም በሽታው በህብረተሠቡ ላይ የሚያስከትለውን ሕመም፣ ሞትና የአካል ጉዳት የህብረተሰቡ ዋነኛ የጤና ችግር ወደማይሆንበት ደረጃ ላይ ማድረስ።

## 3.8.1. የክትትል፤ግምገማ ና ዋና ዋና መለኪያዎች

## 3.8.2. ክትትልና ግምገማ

- ❖ የሚሠበሠቡ መረጃዎችንና የትንተና ውጤቶችን መሠረት በማድረግ በጤና ኬላውና በማህበረሠብ ደረጃ የተከናወኑ ስራዎችን ከተያዘው ዕቅድ ጋር በማነፃፀር መገምገም፤
- ❖ በግምገማው ወቅት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፤ የቀበሌ አመራር አካላትን፤ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን፤ የልማት ቡድንና የ1ለ5 መሪዎችን ማሣተፍ፤
- ❖ በየወሩ በጤና ጣቢያ በሚደረገው የሥራ ግምገማ ላይ በመገኘት በቲቢ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ፕሮግራም አፈጻጸም ዙሪያ የሚታዩ ማነቆዎችን በመለየት የሚፈቱበትን መንገድ መወያየት፤
- ❖ የግምገማውን ውጤት መሠረት በማድረግ ያጋጠሙ ማነቆዎችን ለመፍታት የሚረዱ ተግባራትን በማካተት የዕቅድ ክለሣ ማድረግ
- ❖ ለቲቢ መከላከልና ቁጥጥር ስራዎች የሚያስፈልጉ መድኃቶችና ሌሎች ግብዓቶች ሣይጓደሉ መቅረባቸውን በየወቅቱ መፈተሽ፤ ጉድለቶች በታዩ ጊዜ ከጤና ጣቢያዎችና የወረዳ ጤና ጥበቃ ፅ/ቤቶች ጋር በቅንጅት በመስራት እንዲሟሉ ማድረግ።

- ❖ የተከናወኑ የቲቢ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራትና የተሠጡ የምርመራና ህክምና አገልግሎቶች በወቅቱ በአግባቡ መመዝገባቸውን መፈተሽ፤ ሪፖርቶች በጥራትና በወቅቱ ተጠናቅረው ለሚመለከተው አካል መተላለፋቸውን ማየት።

### 3.8.3. ዋና ዋና አመላካቾች

**የጤና ኬላው ዝግጁነትን በተመለከተ**

- ❖ በማሕበረሰብ አቀፍ ቲቢ መከላከልና ቁጥጥር ዙሪያ የተዘጋጀ ዓመታዊ ዕቅድ
- ❖ የቲቢ መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች አቅርቦት
- ❖ በቲቢ ላይ የተዘጋጁና የተሠራጩ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችና መልዕክቶች

**የቲቢ ህሙማን ልየታን በተመለከተ**

- ❖ በዓመት ውስጥ ከጤና ኬላው ለቲቢ በሽታ ምርመራ ወደ ጤና ጣቢያ የተላኩ ሰዎች ብዛት /ዕድሜ ፣ጾታ/
- ❖ ከጤና ኬላ ለቲቢ ተጠርጥረው ተለይተው ለበለጠ ምርመራ ወደ ጤና ድርጅቶች (ጤና ጣቢያና ሆስፒታል፣ ሌላ የተፈቀደላቸው የምርመራ ማእከላት ) ከተላኩት ውስጥ የቲቢ በሽታ የተገኘባቸው ከመቶኛ (%)
- ❖ በዓመቱ ውስጥ ማንኛውም ዓይነት የቲቢ በሽታ እንዳለባቸው ተረጋግጦ ሕክምና የጀመሩ ሰዎች ብዛት /ዕድሜ፣ ጾታ/፤
- ❖ በዓመቱ ይገኛሉ ከተባሉት የቲቢ ሕሙማን ውስጥ በምርመራ ተለይተው ሕክምና የጀመሩ የቲቢ ታማሚዎች ከመቶኛ(%)

**የቲቢ ሕክምና ውጤቶችን በተመለከተ**

- ❖ ታክመው በአክታ ምርመራ መዳናቸው የተረጋገጠላቸው መጠን ከመቶኛ (%)(Cure Rate)
- ❖ የቲቢ በሽታ ከተራጋገጠላቸው የህክምና ስኬት (ያጠናቀቁና + የዳኑ) ከመቶኛ (TSR among bacteriologically confirmed new TB cases)
- ❖ በዓመት ውስጥ የሕክምና ዉጤታቸዉ ያለታወቀላቸዉ የቲቢ ሕሙማን ብዛት /በቲቢ ዓይነት፣ ዕድሜ ፣ጾታ/ (Not evaluated)
- ❖ በሕክምና ላይ እያሉ ሕይወታቸውን ያጡ የቲቢ ሕሙማን ብዛት /በቲቢ ዓይነት፣ ዕድሜ ፣ጾታ/፤
- ❖ ከተገኙት የቲቢ ሕሙማን ውስጥ ሕክምናቸውን ያጠናቀቁ ብዛት /በቲቢ ዓይነት፣ ዕድሜ ፣ጾታ/
- ❖ ሕክምናቸውን ያቋረጡ የቲቢ ሕሙማን ከመቶኛ (%)
- ❖ ሕክምናው ያልተሳካላቸው (Treatment failure) የቲቢ ሕሙማን ከመቶኛ (%)

## ቁልፍ መልዕክቶች

### የቲቢ በሽታ

የቲዩበርኩሎሲስ በሽታ በአጭሩ የቲቢ በሽታ በመባል ይታወቃል፡፡ የቲቢ በሽታ ካልታከሙት በታማሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያመጣና ሞትን ሊያስከትል የሚችል ነው፡፡ የቲቢ በሽታ በዋነኛነት ሳምባን የሚያጠቃ ቢሆንም ሌሎች የሠውነት ክፍሎችንም ይጎዳል፡፡

የቲቢ በሽታ መንስዔ በዓይን የማይታዩና ባክቴሪያ ተብለው የሚታወቁ ተሕዋሲያን ሲሆኑ ምንጫቸውም በበሽታው የተጠቁና ተገቢውን ህክምና ያልወሠዱ ሠዎች ናቸው፡፡

የቲቢ በሽታ አምጪ ተሕዋሲያን በባህሪያቸው በአየር ላይ በመንሣፈፍ፤በእቃዎች ወይም በወለል ላይ ለጥቂት ሠዓታት በህይወት መቆየት ይችላሉ፡፡ በቂ የአየር ዝውውርና የፀሐይ ብርሃን መኖር የበሽታው አምጪ ተሕዋሲያን ቁጥር የመቀነስ እና በህይወት እንዳይቆዩ የማድረግ አቅም አላቸው፡፡

በቲቢ በሽታ የተጠቃ ግለሠብ በሚያስነጥስ፤ በሚስል፤ በሚናገርበት ወቅት የበሽታው አምጪ ህዋሣትን ወደ አካባቢው አየር ሊረጭ ይችላል፡፡ ሌላ ሠው በተሕዋሲያኑ የተበከለውን አየር ወደ ውስጥ በሚተነፍስበት ጊዜ ህዋሣቱ በአፍና በአፍንጫው በመግባት በቀላሉ ወደ ሣምባው ይደርሣሉ፡፡

በመጀመሪያም ሳምባውን በመበከል በሽታውን ሊያስከትሉ ወይም ወደ ሌሎች የሠውነት ክፍሎች ሊሠራጩ ይችላሉ፡፡ ብዙ ሠዎች የቲቢ በሽታ አምጪ ህዋሣቱ ወደ ሠውነታቸው ቢገቡም ህመም ሣይሠማቸው ወይም የበሽታውን ምልክቶች ሣያሣዩ ለረጂም ጊዜ ሊቆዩ ይችላሉ፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች የሠውነት በሽታን የመከላከል አቅም ሲዳከም እነዚሁ ተህዋሲያን ተራብተው በሽታውን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

### ለቲቢ በሽታ ስርጭት አመቺ ሁኔታዎች

የሚከተሉት ሁኔታዎች የቲቢ በሽታ በስፋት እንዲሠራጭ ምክንያት ይሆናሉ፡-

- በቲቢ በሽታ የተጠቃ ሠው በፍጥነት ምርመራ አድርጎ ህክምናውን ባለመጀመር
- በበሽታው የተያዘ ሠው በሚስልና በሚያስነጥስበት ጊዜ አፍና አፍንጫውን ባለመሸፈን የበሽታውን አምጪ ህዋሣትን ወደ አየር እንዲረጭ በማድረግ
- በጠባብና አየር በበቂ ሁኔታ በማይዘዋወርበት የመኖሪያና የስራ ቦታ ላይ ተፋፍጎ መቆየት
- በጉዞ ወቅት የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን መስኮት አለመክፈት
- በደማቸው ውስጥ የኤች.አይ.ቪ. ያለባቸው ሠዎች በተለየ ሁኔታ ለበሽታው ስለሚጋለጡ ተገቢውን ጥንቃቄ አለማድረግ

### ለቲቢ በሽታ በተለየ የሚያጋልጡ ሁኔታዎች

ሁሉም የህብረተሠብ ክፍል በቲቢ በሽታ የሚያዝ ቢሆንም ህፃናት፤ልጆች እና አዛውንቶች፤ ህክምና የማይከታተሉ የስኳር በሽታ ተጠቂዎች እና በሌሎች ሁኔታዎች በሽታን የመከላከል አቅማቸው ዝቅተኛ

የሆኑ ሠዎች በቲቢ በሽታ የመጠቃት እድላቸው ከሌላው የህብረተሠብ ክፍል ከፍ ያለ ነው፡፡

**የቲቢ በሽታ ዋነኛ ምልክቶች**

- ሣል
- የደረት ውጋት/ህመም
- የድካም፤የመጫጫን ወይም የሠውነት መዛል ስሜት
- የምግብ ፍላጎት መቀነስ
- የሠውነት ክብደት መቀነስ
- የሠውነት ሙቀት መጨመር/ሌሊት በላብ መዘፈቅ ሲሆኑ በበሽታው እንደተጠቃው የሠውነት አካል ሌሎች ምልክቶችም ሊታዩ ይችላሉ፡፡

**የቲቢ በሽታ ምርመራ**

ቲቢ በሽታ ሊኖርባቸው ይችላል ተብለው የሚገመቱ ህሙማን በሙሉ የአክታ ምርመራ የሚደረግላቸው ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ለአንዳንድ ህሙማን ሌሎች ምርመራዎችም ሊደረጉ ይችላሉ፡፡

**የቲቢ በሽታ ህክምና**

ቲቢ በህክምና የሚድን በሽታ ነው፡፡ አብዛኞቹ የቲቢ ህሙማን በየዕለቱ በአፍ የሚወሠዱ እንክብሎች ለተከታታይ ስድስት ወራት እንዲወስዱ በጤና ባለሙያ ይታዘዝላቸዋል፡፡ አንዳንድ ህሙማን ደግሞ እንደበሽታቸው ሁኔታ ከስድስት ወራት በላይ ለሚቆይ ጊዜ መድኃኒቶቹን እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡ የቲቢ መድኃኒት በመርፌ መልክ የታዘዘላቸው ህሙማንም መድኃኒቱን ሳያቋርጡ መከታተል ይኖርባቸዋል፡፡ በጤና ባለሙያ የታዘዘላቸውን የቲቢ ህክምና መድኃኒት በአግባቡ የወሠዱ ህሙማን ከበሽታቸው ይፈወሣሉ፡፡

**መድሃኃትን የተላመደ ቲቢ**

የቲቢ ህሙማን የታዘዘላቸውን መድኃኒት በየዕለቱ በታዘዘላቸው መጠን በአግባቡ ሣይወስዱ ሲቀሩ መድኃኒትን የተላመደ የቲቢ በሽታ ሊከሠት ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜም በዚህ በሽታ ዓይነት አስቀድመው ከተያዙ ሠዎች በመተላለፍ ሊይዝ ይችላል፡፡

መድኃኒትን የተላመደ ቲቢ የሚተላለፍባቸው መንገዶችና በበሽታው የተጠቁ ህሙማን የሚያሣይዋቸው ምልክቶች ከቲቢ በሽታ ጋር ተመሣሣይና በፍፁም የማይለዩ ናቸው፡፡ ይህንን የበሽታ ዓይነት የሚያመጡት ህዋሣት (ባክቴሪያ) ለወትሮው የሚታዘዙትን የቲቢ መድኃኒቶችን በመላመዳቸው ምክንያት ይህንን በሽታ ለማከም የሚታዘዙት መድኃኒቶች ሌላ ዓይነት ሆነው የሚሠጡትም እስከ ሁለት ዓመት ለሚቆይ ግዜ ነው፡

**ቲቢንና መድኃኒቱን የተላመደ ቲቢ በሽታን ለመከላከል የሚወሠዱ ጥንቃቄዎች**

- የቲቢ በሽታ ምልክት ያለባቸው ሠዎች ጊዜ ሣይወስዱ ወደ ጤና ተቋም በመሄድ ምርመራ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
- ሠዎች በሚስሉበት፤ በሚያስነጥሱበት ጊዜና ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚናገሩበት ጊዜ

አፋቸውን በመሀረብ ወይም በጨርቅ መሸፈን አለባቸው፡፡

- በቲቢ በሽታ መጠቃታቸው በጤና ባለሙያ ተረጋግጦ መድኃኒት የታዘዘላቸው ሠዎች መድኃኒታቸውን በአግባቡ መውሠድ አለባቸው፡፡
- መስኮቶችንና በሮችን ክፍት አድርጎ በቂ አየር እና የፀሐይ ብርሃን እንዲገባ በማድረግ በአካባቢው ሊኖሩ የሚችሉትን የቲቢ አምጪ ተሕዋሲያን መቀነስና አቅም ማዳከም ይቻላል፡፡
- የቲቢ ሕመምተኞች አክታቸውን ክዳን ባለው ዕቃ አጠራቅመው ቆፍረው መቅበር ይህ ካልተቻለ ግን ከነዕቃው ማቃጠል ይኖርባቸዋል፡፡

**የቲቢ መድኃኒት ቀላል የጎንዮሽ ጉዳቶች፡-**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የቲቢ መድኃኒት ቀላል የጎንዮሽ ጉዳቶች ያጋጠሙአቸው ታካሚዎች በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ሙያዊ ምክርና የመድኃኒት ህክምና ይሠጣቸዋል፡፡

- የምግብ ፍላጎት መቀነስ
- የማቅለሽለሽ ስሜትና ማስመለስ
- መጠነኛ የሆድ ህመም
- የመገጣጠሚያዎች ህመም
- የመዳፍና የውስጥ እግር ማቃጠል
- የማሣከክ ስሜት እና ሽፍታ
- የሽንት ቀለም መቅላት

**ከፍተኛ የጤና ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ የቲቢ መድኃኒት የጎንዮሽ ጉዳቶች፡-**

- ነጩ የአይን ክፍል ቢጫ መሆን
- ከባድ የሆድ ህመም
- በቆዳ ላይ ሽፍታ መታየት
- የማየት ችግር
- የመስማት ችግር
- ከላይ የተዘረዘሩት የቲቢ መድኃኒት የጎንዮሽ ጉዳቶች የታዩባቸው ህሙማን ወደ ጤና ጣቢያ በመሄድ ተጨማሪ ምርመራና ህክምና እንዲሠጣቸው ያስፈልጋል፡፡

# ክፍል ሁለት፡ የስጋደዌ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር መርሐ ግብር

## 1. መግቢያ

የሥጋ ደዌ በሽታ መንስኤው ማይኮባክቴሪየም ሌፕሬ ተብሎ የሚጠራ የባክቴሪያ ዝርያ ሲሆን አምራች የሆነውን የሕብረተሰብ ክፍል የሚያጠቃ ተላላፊ በሽታ ነው። የሥጋ ደዌ በሽታ የሚታወቀው በወቅቱ ካልታከሙት የአካል ጉዳት በማስከተሉና በግንዛቤ እጥረት የተነሳ በጉዳተኞች ላይ በሚያደርሰው መገለል ነው። በሥጋ ደዌ ዙሪያ የቅርብ ጊዜ ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት በሽታው ጎልቶ የሚታየው በተወሰኑ አካባቢዎች ውስጥ ነው፡ ፡

በስጋ ደዌ በሽታ ምክንያት የአካል ጉዳት የሚደርስባቸው ህሙማንና በበሽታው የሚያዙ ህፃናት ቁጥር ከፍተኛ መሆን የህክምና አገልግሎቱና የቁጥጥሩ ስራ በሚገባ ለተጠቃሚው ህብረተሠብ አለመድረሱንና በሽታው በህብረተሠቡ ውስጥ መሠራጨት መቀጠሉን ይጠቁማል።

የስጋ ደዌ በሽታ ስርጭትን ለመግታትና ዋነኛ የጤና ችግር እንዳይሆን ለማድረግ ብሎም ከአገሪቱ ለማጥፋት ሽታው በንፅፅር በስፋት የሚገኝባቸውን አካባቢዎች ለይቶ የተጠናከረ የመከላከል እንዲሁም ህሙማኑን ፈልጎ የማከም ስራ መሠራት ይኖርበታል። በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ በሽታው አንሠራርቶ እንደገና የህብረተሠቡ ዋነኛ የጤና ችግር እንዳይሆን ከመከላከሉ ስራ በተጨማሪ የማያቋርጥ የህሙማን ልየታና ህክምና ስራ መሠራት አለበት።

በአጠቃላይ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች በማህበረሠብ ደረጃ የተጠናከረ የስጋደዌ መከላከልና ቁጥጥር ስራ ለህሙማኑም የህክምናና ክትትል አገልግሎትን በተጠናከረ መንገድ መሥጠት የሚያስፈልግ ሲሆን ከዚህ ስራ ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስዱት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችና ህብረተሠቡ ናቸው። የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የማህበረሠብ አቀፍ ስራውን የመምራት፤ የማስተባበርና የመፈፀም ኃላፊነት መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

## 2. ዓላማ

### 2.1. አጠቃላይ ዓላማ

ህብረተሠቡን በማሣተፍ የስጋደዌ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራትን በማከናወንና ለስጋደዌ ህሙማን እንክብካቤ በማድረግ የበሽታውን ሥርጭት መግታት፣ በሽታው የሚያደርሰውንም ሕመም፣ ሞትና የአካል ጉዳት መቀነስ፤ መቆጣጠር ብሎም በቀጣይ የህብረተሰቡ ችግር ከማይሆንበት ደረጃ ላይ ማድረስና ማጥፋት ነው፡፡

#### 2.1.1. ዝርዝር ዓላማዎች

- ❖ ህብረተሰቡ በስጋ ደዌ በሽታ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግና በመከላከልና ቁጥጥር ሥራው ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆን እንዲሁም ለበሽታው ተጠቂዎች እንክብካቤ እንዲያደርግና ፍቅር እንዲሠጥ ማስቻል፤
- ❖ የስጋደዌ በሽታ ምልክት የታየባቸው ሰዎችን በቶሎ በመለየትና አገልግሎቱ ወደሚገኝበት ጤና ተቋም በመላክ ተገቢውን ምርመራና ህክምና እንዲያደርጉ ማስቻል፣
- ❖ በስጋደዌ በሽታ ምክንያት የአካል ጉዳት የደረሠባቸው የህብረተሠብ ክፍሎች የስነ ልቦናና ሌሎች ድጋፎች የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት
- ❖ ለበሽታው የተጋለጡ የስጋደዌ ሕሙማን ቤተሰቦች ተገቢውን የስጋደዌ በሽታ ምርመራና ክትትል እንዲያገኙ ማድረግ፤
- ❖ የስጋደዌ ዕለታዊ የመድኃኒት ሕክምናና ክትትል አገልግሎትን በሁሉም ጤና ኬላዎች እንዲሰጥ በማድረግ አገልግሎቱን የበለጠ ተደራሽና ስኬታማ ማድረግ፣
- ❖ የስጋደዌ ሕክምና እና ክትትል አገልግሎቱን በማጠናከር የህክምና ውጤቱ የተሣካ እንዲሆን ማድረግ፤
- ❖ በማህበረሰብ ደረጃ የሚከናወኑትን የስጋደዌ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራትን እንዲሁም የሚሠጡትን የስጋደዌ ምርመራ፤ ህክምናና ክትትል አገልግሎቶችን በመመዝገብ፤ መረጃዎችን በመተንተንና ሪፖርቶችን በማጠናቀር ለውሣኔ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፤

## 3. ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራትና አተገባበር

### 3.1. የሥጋ ደዌ በሽታ መጠንና ስርጭት ያገናዘበ የመከላከል፣ቁጥጥር፣ ሕክምና የህሙማን ክብካቤ ዕቅድ ማዘጋጀትና መፈፀም

- ❖ በማህበረሠብ ደረጃ የሚገኙ የሥጋ ደዌ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር መርሐ ግብርን ለማቀድና አፈፃፀሙን ለመከታተል የሚረዱ የጤናና የሥነ ሕዝብ መረጃዎችን ማሰባሰብ፤ ማደራጀትና መተንተን፤

- ቀደም ባሉ ጊዜያት በአካባቢው የተለዩ የሥጋ ደዌ ህሙማንን ዝርዝር መረጃ መሠብሠብ፤ ማደራጀትና መተንተን፤ ውጤቱንም ለዕቅድ ዝግጅት በግብዓትነት መጠቀም፤
- ከጤናው ዘርፍና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ሊቀርቡ የሚችሉ ግብአቶችን መረጃ ማሰባሰብና መተንተን፤ ውጤቱንም ለዕቅድ ዝግጅት በግብዓትነት መጠቀም፤
- የመረጃ ትንተና ውጤትን መሠረት በማድረግ የሥጋ ደዌ መከላከልና መቆጣጠር ስራዎችን እንዲሁም የሥጋ ደዌ ህሙማን እንክብካቤ ዕቅድ ማዘጋጀት፤
- ከህብረተሠቡና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ዕቅዱን መፈፀም፤ አፈፃፀሙን መከታተልና መገምገም

## 3.2. ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን ማከናወን

- የተለያዩ ሥልቶችን በመጠቀም ለሥጋ ደዌ ሕሙማን፣ ለቤተሰቦቻቸውና ለህብረተሰቡ ስለሥጋ ደዌ በሽታ መንሥዔ፣ መተላለፍያ መንገድ፣ መከላከልና መቆጣጠር ተግባራት ላይ ተከታታይነት ያለው ትምህርት መስጠት፣
- የስጋደዌ በሽታ በተነፃፃሪ በስፋት በሚገኝባቸው አካባቢዎች ህብረተሠቡ ለስጋደዌ ህሙማኑ መስጠት ስለሚገባቸው እንክብካቤና ድጋፍ ተከታታይነት ያለው ትምህርት መስጠት፤
- በሥጋ ደዌ መድኃኒት አወሳሰድና በበሽታው ቁጥጥር ዙሪያ ለሕሙማን ቤተሰብ አባላት፣ ለ1ለ5 መሪዎች ሥልጠና መስጠትና አፈጻጸሙን መከታተል፤
- በትምህርት ቤቶች፤ በልማት ተቋማት፤ በማረሚያ ቤቶች በመገኘት ለተቋሙ ህብረተሠብ በሥጋ ደዌ በሽታ መተላለፊያ መንገዶች፤ የበሽታው ምልክቶች፤ ህክምናውና መከላከያ መንገዶቹ ላይ ያተኮረ የጤና ትምህርት መስጠት፤
- መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት አባላትና ሠራተኞች በሥጋ ደዌ መከላከልና ቁጥጥር ላይ ያተኮረ የጤና ትምህርት መስጠት፤

**የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይቶች የሚካሄዱባቸው ቦታዎችና ሁኔታዎች፡**

- በቤት ለቤት ጉብኝት ወቅት
- ህብረተሠቡ የጤና አገልግሎት ለማግኘት ወደ ጤና ኬላ በሚመጣበት ወቅት
- ከስጋደዌ በሽታ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ውይይት በሚካሄድበት ወቅት ለምሣሌ፤ ቲቢ፤ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች…ወዘተ
- በተለያዩ ስብሠባዎች ላይ
- በገበያ ቦታዎች ላይ
- በአንድ ለአምስትና የጤና ልማት ቡድን ስብሠባዎች ላይ
- በትምህርት ቤቶች፤ ማረሚያ ቤቶች

### 3.3. የሥጋደዌ በሽታ ምልክቶች ያለባቸው ሰዎችን በመለየት ምርመራ እንዲያገኙ ማድረግ፤

- የልማት ቡድኖች፤ የ1ለ5 ትስስር አባላት በአጠቃላይ ማህበረሠቡ የለዩአቸውን የሥጋ ደዌ በሽታ ምልክት ያሉባቸውን ሠዎች በጤና ኬላ ተቀብሎ ለሥጋ ደዌ በሽታ ምርመራ ማድረግና ተጨማሪ ምርመራ የሚያስፈልጋቸውን በመለየት ወደ ጤና ተቋም መላክ

- በቤት ለቤት ጉብኝት፤ በገበያ ቦታዎች፤ በትምህርት ቤቶች፤ በእምነት ተቋማት፤ በማረሚያ ቤቶች፤ በልማት ተቋማት ወዘተ… በሚሄዱበት ወቅት የለዩዋቸውን የሥጋ ደዌ ምልክቶች ያሉባቸውን ሰዎች ለምርመራ ወደ ጤና ተቋም መላክ፤

#### 3.3.1. ከሕሙማን ጋር አብረው በመኖራቸው ምክንያት ለሥጋ ደዌ በሽታ የተጋለጡ ሰዎችን የምርመራ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፡

- ከሥጋ ደዌ ሕሙማን ጋር የሚኖሩ የቤተሰብ አባላትን መጎብኘትና የበሽታው ምልክት ያሉባቸውን ሠዎች በመለየት መመርመር፤

- የሥጋ ደዌ በሽታ ምልክት ለሚያሳዩና ተጨማሪ ምርመራ የሚያስፈልጋቸውን የሥጋ ደዌ ታማሚ ቤተሰብ አባላት በመለየት ወደ ጤና ተቋም መላክ፣

#### 3.3.2. የሥጋ ደዌ ሕሙማን ተገቢውን ሕክምና በአቅራቢያቸው እንዲያገኙ ማድረግና መከታተል፣

- በሥጋ ደዌ በሽታ እንደተያዙ ተረጋግጦ መድኃኒት የታዘዘላቸው ታካሚዎች መድኃኒታቸውን በየዕለቱ መውሰዳቸውን መከታተል፤

- ሕክምና ላይ ያሉ የስጋደዌ ሕሙማንን ወደ መኖሪያ ቤታቸው በመሄድ የጤንነታቸውን ሁኔታ መቆጣጠር እንዲሁም ለሚታይባቸዉ የጤና ችግር ዕርዳታ እንዲደረግላቸው ወደ ጤና ጣቢያ በመላክ ግብረ መልስ መቀበል፤

- ህክምና ላይ የሚገኙ የስጋደዌ ህሙማን በቀጠሮ ጊዜያቸው ህክምናቸውን ወደሚከታተለው ጤና ተቋም እንዲሄዱ ማድረግና አገልግሎቱን ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤

- የስጋደዌ ታካሚዎች ከሚወስዱት መድኃኒት ጋር በተያያዘ ቀላል ወይም ከባድ የሆነ የመድኃኒት የጎንዮሽ ችግር መከሰት አለመከሰታቸውን መከታተል፤ ከተከሰቱ በመመሪያው መሠረት መወሰድ የሚገባውን እርምጃ መውሰድ፣ለተሻለ ህክምና ወደ ጤና ጣቢያ መላክ፤

- የሥጋ ደዌ ሕሙማን በበሽታው ምክንያት ሊያጋጥማቸው የሚችለውን ተጨማሪ የአካል ጉዳት ለመከላከል የሚያስችል እንክብካቤ ማድረግ፤

- ታካሚዎች የአድራሻ ለውጥ የሚያደርጉ ከሆነ በሚሄዱበት ቦታም ሲደርሱ ሕክምናቸዉን ሳያቋርጡ መቀጠል እንዲችሉ መሸኛ እንዲዘጋጅላቸው ሕክምናቸውን ወደ ጀመሩበትና ክትትል ወደሚያደርጉበት ጤና ጣቢያ መልሶ መላክ፤

- ሕክምና የጀመሩ የስጋደዌ ሕሙማን ሕክምናቸውን ቢያቋርጡ ወደ መኖሪያ ቤታቸው በመሄድና በመወያየት ሕክምናቸውን እንዲቀጥሉና እንዲያጠናቅቁ ድጋፍ ማድረግ፤

- በስጋደዌ በሽታ ምክንያት የአካል ጉዳት የደረሠባቸውን ሠዎች በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች ለመደገፍ በሚደረጉ ስራዎች ላይ በንቃት መሣተፍ

# 4. አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

## 4.1. የህክምና ግብዓቶችና ሌሎች ቁሣቁሶች

በጤና ኬላ ደረጃ የሚከናወኑ የስጋ ደዌ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ስራዎችና የሚሠጡት አገልግሎቶችን በተቀላጠፈና ጥራቱን በጠበቀ መንገድ ለማከናወን የሚደግፉ ሠነዶች፡

- የማዳመጫ መሣሪያ (Stethoscope)
- የደም ግፊት መለኪያ መሣሪያ
- የሠውነት ሙቀት መለኪያ
- የክብደት መለኪያ ሚዛን
- ለስጋደዌ ህክምና የሚሠጡ መድሃኒቶች በየዕለቱ የሚወሠዱ በመሆኑና ታካሚዎች በቀጠሯቸው ወቅት ለወር የሚበቃ መድኃኒት ከጤና ጣቢያ ስለሚያገኙና በቤታቸው ሆነው በየዕለቱ መውሠድ ስለሚችሉ በጤና ኬላ ደረጃ እነዚህን መድኃኒቶችን ማዘጋጀት አስፈላጊ አይደለም፡፡
- የማህበረሠብ አቀፍ የስጋ ደዌ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር አተገባበር መመሪያ፣
- ለልማት ሠራዊት አባላት፤ ለስጋ ደዌ ህሙማን፣ ለቤተሠቦቻቸውና ለትምህርት ቤቶች የተዘጋጀ አጭር መፅሐፍና በራሪ ፅሁፍ፣
- ለአዋቂዎችና ለህጻናት በውህድ መልክ የተዘጋጁ የስጋ ደዌ መድኃኒቶች ዓይነትና መጠን የምገልፅ ሠንጠረዥ፣
- በስጋ ደዌ በሽታ ላይ መልዕክት ለማስተላለፍ የተዘጋጀ ፖስተር፣

## 4.2. የጤና ጣቢያ ጤና ኬላ ትስስር

በስጋ ደዌ በሽታ ምርመራ የቆዳ ናሙና የላቦራቶሪ ምርመራ ስለሚያስፈልገውና የበሽታው ምልክት ያሉባቸው ሠዎች ልምድ ባላቸው የጤና ባለሙያዎች መመርመር ስለሚያስፈልጋቸው ጤና ኬላዎች እንደነዚህ ያሉ ህሙማንን ወደ ደጋፊው ጤና ጣቢያ መላክ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ጤና ኬላዎች ለተጨማሪ ምርመራ የላኳቸውን ህሙማን አገልግሎቱን ማግኘታቸውን ይከታተላሉ፤ በምርመራው ውጤት መሠረት የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ከጤና ጣቢያው ጋር በቅንጅት ይሠራሉ፡፡ ጤና ጣቢያዎች በትስስሩ

ለሚደግፏቸው ጤና ኬላዎች ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት የሚመደቡ ባለሙያዎችም በጤና ኬላ ደረጃ የሚሠጡ የስጋደዌ ህሙማን ህክምናና ክትትል አገልግሎቶች ጥራታቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ሙያዊ ድጋፍ ይሠጣሉ፡፡

ጤና ጣቢያዎች የስጋደዌ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር ተግባራትን አስመልክቶ በጤና ኬላ የተከናወኑ ስራዎችን ሪፖርት በየወቅቱ ተረክበው ይተነትናሉ፤ ከሚደግፏቸው ጤና ኬላዎች ጋር በመሆን አፈፃፀሙን ይገመግማሉ፤ ለአፈፃፀሙ መሻሻል የሚረዱ የእርምት ተግባራትን ይጠቁማሉ፤ መተግበራቸውንም ይከታተላሉ፡፡

## 4.3. የሚጠበቅ ውጤት

በጤና ኬላ ደረጃ የሚያስፈልጉ የሠው ኃይልና ሌሎች ግብዓቶች እንዲሟሉ በማድረግ እንዲሁም ተገቢውን ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት ጤና ኬላው የሚከተሉትን ውጤቶች እንዲያሣካ ይጠበቃል፡-

- ህብረተሠቡ የስጋደዌ በሽታ ስርጭትን ለመግታት የመከላከያ ዘዴዎችን ይተገብራል፤ በበሽታው ለተጠቁ ሠዎችም ድጋፍና እንክብካቤ ያደርጋል፤
- ወደ ጤና ተቋም በመሄድ የስጋደዌ በሽታ ምርመራና ህክምና አገልግሎት የሚያገኙ ሠዎች ቁጥር ይጨምራል፤
- በስጋደዌ የተጠቁ ሠዎች በበሽታው ምክንያት ከፍተኛ የአካል ጉዳት ሣይደርስባቸው በፍጥነት ህክምና ይጀምራሉ፤ በበሽታው የአካል ጉዳት የሚደርስባቸው ሠዎች ቁጥር ይቀንሣል፤
- በስጋደዌ በሽታ የሚጠቁ ህፃናትና ልጆች ቁጥር ይቀንሣል
- የስጋደዌ ህሙማን ቤተሠቦች በሙሉ ለስጋደዌ በሽታ ምርመራ አገልግሎት ያገኛሉ
- የስጋደዌ ህክምና የጀመሩ ህሙማን በሙሉ ህክምናቸውን በተሣካ ሁኔታ ያጠናቅቃሉ
- የስጋደዌ በሽታ ተጠቂዎች ላይ የሚደርሠው አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት ተቀንሶ አምራች ዜጋ ይሆናሉ፤

በአጠቃላይ የስጋደዌ በሽታ ስርጭትን በመከላከል ህሙማንን በወቅቱ በመለየት፤ በመመርመርና በማከም በሽታው በህብረተሠቡ ላይ የሚያስከትለውን ሕመም፣ ሞትና የአካል ጉዳትየሕብረተሰቡ ዋነኛ የጤና ችግር ወደ ማይሆንበት ደረጃ ላይ ማድረስና በመጨረሻም ማጥፋት

## 4.4. የክትትልና ግምገማ፤ የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ዋና ዋና አመላካቾች

### 4.4.1. ክትትልና ግምገማ

- የሚሠበሠቡ መረጃዎችንና የትንተና ውጤቶችን መሠረት በማድረግ በጤና ኬላውና በማህበረሠብ ደረጃ የተከናወኑ ስራዎችን ከተያዘው ዕቅድ ጋር በማነፃፀር መገምገም፤
- በግምገማው ወቅት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፤ የቀበሌ አመራር አካላትን፤ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን፤ የልማት ቡድንና የ1ለ5 መሪዎችን ማሣተፍ፤
- በየወሩ በጤና ጣቢያ በሚደረገው የሥራ ግምገማ ላይ በመገኘት በስጋ ደዌ መከላከልና ቁጥጥር ፕሮግራም አፈጻጸም ዙሪያ የሚታዩ ማነቆዎችን በመለየት የሚፈቱበትን መንገድ መወያየት፤
- የግምገማውን ውጤት መሠረት በማድረግ ያጋጠሙ ማነቆዎችን ለመፍታት የሚረዱ ተግባራትን በማካተት የዕቅድ ክለሣ ማድረግ
- ለስጋ ደዌ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ስራዎች የሚያስፈልጉ መድኃቶችና ሌሎች ግብዓቶች ሣይጓደሉ መቅረባቸውን በየወቅቱ መፈተሽ፤ ጉድለቶች በታዩ ጊዜ ከጤና ጣቢያዎችና የወረዳ ጤና ጥበቃ ፅ/ቤቶች ጋር በቅንጅት በመስራት እንዲሟሉ ማድረግ፡፡
- የተከናወኑ የስጋ ደዌ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራትና የተሠጡ የምርመራና ህክምና አገልግሎቶች በወቅቱ በአግባቡ መመዝገባቸውን መፈተሽ፤ ሪፖርቶች በጥራትና በወቅቱ ተጠናቅረው ለሚመለከተው አካል መተላለፋቸውን ማየት፡፡

### 4.4.2. የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት ዋና ዋና አመላካቾች

**የጤና ኬላው ዝግጁነትን በተመለከተ**

- በጤና ኬላና በማሕበረሰብ ደረጃ የሚከናወኑ የስጋደዌ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ስራዎችን ያካተተ ዓመታዊ፤ የሩብ ዓመትና ወርሃዊ ዕቅድ መኖር
- ለስጋደዌ መከላከልና መቆጣጠር ስራዎች ለመመዝገብና ህሙማንን ለመላክ የሚያስፈልጉ መዝገብና ቅፆች መኖር
- በስጋደዌ ላይ የተዘጋጁ መልዕክቶችን የያዙ የማስተማሪያና መርጃ መሣሪያዎች መኖር
- በስጋደዌ ላይ የተካሄዱ ውይይቶችና የጤና ትምህርቶች ብዛት

**የስጋደዌ በሽታተጠቂዎችን ለይቶ ማግኘትና ህክምና ማስጀመርን በተመለከተ**

- በጤና ኬላ ደረጃ የስጋደዌ በሽታ ምርመራ የተደረገላቸው ሠዎች ብዛት /ዕድሜ ፣ ጾታ/
- ከጤና ኬላ ለምርመራ ወደ ጤና ጣቢያ የተላኩ የስጋደዌ በሽታ ምልክት ያለባቸው ሠዎች ብዛት /ዕድሜ ፣ጾታ/
- ከጤና ኬላ ለበለጠ ምርመራ ወደ ሌሎች ጤና ድርጅቶች ከተላኩት ውስጥ የስጋደዌ በሽታ የተገኘባቸው ህሙማን ብዛት (በቁጥርና በመቶኛ)
- የስጋደዌ በሽታ እንዳለባቸው ተረጋግጦ ሕክምና የጀመሩ ሰዎች ብዛት /ዕድሜ፣ ጾታ/፤

**የስጋደዌ በሽታ ሕክምና ውጤቶችን በተመለከተ**

- ህክምናቸውን በአግባቡ ወስደው መዳናቸው በሚከታተላቸው ጤና ተቋም የተረጋገጠላቸው የስጋደዌ ታካሚዎች (በቁጥርና በመቶኛ)
- ሕክምናቸውን በአግባቡ ተከታትለው ያልጨረሱና መዳናቸው ያልተረጋገጠላቸው የስጋደዌ ህሙማን (በቁጥርና በመቶኛ)